የሰ/መ/ቁጥር 239034 እና 239035

ህዳር 27 ቀን 2016 ዓ/ም

ዳኞች፡-እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካች፡- ወ/ሮ ማሪቱ ሁሴን ---------አልቀረቡም

ተጠሪ፡- አቶ ፍሰሀ አሰፋ ---------- አልቀረቡም ከተባለ በኋላ ጠበቃ መሰለ አቡን ቀረበ

የሰ/መ/ቁ.239034 እና 239035 የተቀጠሩት ለምርመራ ሲሆን በዚሁ አግባብ መዝገቦቹ ተጣምረው ተመርምረው የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች በሰ/መ/ቁ.239034 ታህሳስ 18 ቀን 2015 ዓ.ም እንዲሁም በሰ/መ/ቁ.239035 በተመሳሳይ ቀን ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጲያ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 11792 በ28/03/2015 ዓም በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በማፅናት እንዲሁም በሰ/መ/ቁ.11306 በ28/03/2015 ዓም በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በማሻሻል የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለታቸው ሲሆን አመልካች በስር

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ለነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ፍ/ቤት ተከሳሽ ሆነው ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ ሆነው ከጋብቻ ውጪ እንደ ባልና ሚስት የመኖር ግንኙነት መቋረጥን ተከትሎ በመጣው የንብረት ክፍፍል ክስ ጉዳይ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እንዲህ ነው፡-ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ በአማን ክፍለ ከተማ ውስጥ የሚገኘውን አዋሳኙ በክሱ ውስጥ የተመለከተውን አንድ ደጃፍ ቤት በውስጡ ሳሎን፣መኝታ ቤትና እቃ ቤት ያለበት፣ሁለተኛ ደጃፍ ቤት ተመሳሳይ አይነት ክፍሎችን የያዘ፣አራት በአራት ሰርቪስ ቤት፣ሽንት ቤት እና ኩሽና በግሌ የሰራኋቸውን በስራ ምክንያት ከአማን ከተማ ስወጣ ለወ/ሮ ኢትዮጲያ ሞላ እና አቶ ልመንህ አለሙ በተለያየ ጊዜ ውክልና በመስጠት ሲያስተዳድሯቸው የቆዩትን ቤቶች ከአመልካች ለወለድኳት ልጃችን ቀለብ እንድከፍል ሲወሰን የቤቱን ኪራይ ተቀብላ ለልጃችን ቀለብ እንድታውል በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት የቤት ኪራዩን ስትቀበል ከቆየች በኋላ ከ2012 ዓም ጀምሮ በቤቱ ውስጥ ገብታ መኖር የጀመረች በመሆኑ ቤቱን ከነእቃው ለቃ እንድትወጣ ይወሰንልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

አመልካች በሰጡት መልስም ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበው ከመከራከራቸው በተጨማሪ ቤቱ የተጠሪ የግል ንብረት ሳይሆን የጋራ ሀብታችን ነው፣ከ1983 ዓም እስከ 1993 ዓም ከጋብቻ ውጪ እንደ ባልና ሚስት ስንኖር ከ1983 ዓም እስከ 1985 ዓም ባለው ጊዜ ውስጥ ዋናውን ቤት ከአንድ ሰርቪስ ጋር የሰራነው በመሆኑ የጋራ ሀብት ነው ተብሎ ይወሰንልን በማለት በፍሬ ጉዳዩ ላይ መከራከራቸውን የስር ፍርድ ቤት መዝገብ ያሳያል፡፡አመልካች ከዚህ በተጨማሪ ባቀረቡት የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ከጋብቻ ውጪ እንደ ባልና ሚስት የመኖር ግንኙነቱ ከተቋረጠ በኋላ ቤቱን ከ10 ዓመት በላይ በመያዝ በግሌ 3 ክፍል ሰርቪስ ቤት ግምቱ ብር 400,000.00 እና ኩሽና፣አጥር፣ሽንት ቤት፣ሻወር ቤትና ሴፕቲክ ታንክ ግምታቸው ብር 200,000.00 የሰራሁ በመሆኑ እነዚህ ንብረቶች የግል ሀብቴ መሆናቸው ተረጋግጦ ይወሰንልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

አመልካች ላቀረቡት የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ተጠሪ በሰጡት መልስም አመልካች ስድስት መቶ ሺህ ብር የሚያወጣ ግንባታ አላከናወኑም፣ገንብቼያለሁ ቢሉ እንኳ በይዞታዬ ላይ እኔ ሳልፈቅድ ያከናወኑት በመሆኑ ምንም መብት የላቸውም ተብሎ ይወሰንልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

የስር ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን በቃል አከራክሮ ምስክሮችን ሰምቶ፣የሰነድ ማስረጃዎችን መርምሮ እና በቦታው ተገኝቶ ምልከታ አድርጎ በሰጠው ውሳኔም አመልካች ከተጠሪ ጋር ከ1983 ዓም እስከ 1994 ዓም ከጋብቻ ውጪ እንደባልና ሚስት መኖራቸውን ማስረዳታቸውን፣ይዞታውን ተጠሪ በ1982 ዓም በምሪት ወስደው ከ1983 ዓም እስከ 1985 ዓም ባለው ጊዜ ውስጥ ሰርተው ሲያጠናቅቁ ከጋብቻ ውጪ እንደ ባልና ሚስት ሲኖሩ የነበረ ቢሆንም የደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መንግስት የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ.75/1996 ዓም የወጣው ግንኙነቱ ከተቋረጠ በኋላ በመሆኑ ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት የሌለው በመሆኑ የግራ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ለነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ቀኙ ክርክር መታየት የሚገባው ከፍ/ብ/ህ/ቁ.712 አንፃር መሆኑን ይህ ድንጋጌ ደግሞ በግንኙነቱ ለተፈፉ ንብረቶች የተጋሪነት መብትን የሚሰጥ ባለመሆኑ ሁለቱ ደጃፍ ቤቶች የተጠሪ የግል ሀብት ናቸው በማለት ወስኗል፡፡

የተከሳሽ ከሳሽነት ክሱን በተመለከተም አመልካች ወደ ቤቱ ገብተው መኖር የጀመሩት ከ2005 ዓም በፊት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ መሆኑን፣በዚህ ጊዜ ውሥጥም ለሁለት ክፍልች ሲሚንቶ ማስገባታቸውን፣የበረንዳውን ክፈፍና ቆርቆሮ ማስቀየራቸውን፣በር ማሰራታቸውን፣13 ሜትር ቡሩንዳዮ ማስገጣማቸውን፣ሶስት ክፍል ደረጃውን የጠበቀ ቤት በሲሚንቶ ማሰራታቸውን፣ደረጃውን የጠበቀ ሽንት ቤት፣ሴፕቲክ ታንክ ማሰራታቸውን እንዲሁም አጥር በቆርቆሮ ማሰራታቸውን ምስክሮቻቸው ሲያስረዱ የተጠሪ ምስክሮች አለማስተባበላቸውን በመስክ ምልከታው ወቅትም ተጠሪ የዋናውን ቤት በረንዳ ቆርቆሮ መቀየራቸውን ፣ክፈፉንም ማሰራታቸውን 4በ4 የሆነውን ሰርቪስ ቤት አፍርሰው ሶስት ክፍል ሰርቪስ፣ሽንት ቤት፣ሻወር ቤትና ሴፕቲክ ታንክ መስራታቸውን እንደሚያውቁ ተጠሪ መግለፃቸው እነዚህ ግንባታዎች በአመልካች መከናወናቸውን እንደሚያረጋግጡ ጠቅሶ የነዚህ ግንባታዎች ግምት በሚዛን አማን ከተማ ማዘጋጃ ቤት ብር 687,251.20 ሲገመት ተጠረ አለመቃወማቸውን ጠቅሶ ግንባታውንም ሆነ ማሻሻያዎቹን አመልካች ሲያከናውኑ ተጠሪ እያወቁ ዝም ማለታቸው በቤቱ ላይ አመልካች ማንኛውም ማሻሻያ እንዲያደርጉ መፍቀዳቸውን ያሳያል በማለት ግምቱን ተጠሪ ለአመልካች ሊከፍሉ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.10947 ያቀረቡ ቢሆንም ሚያዝያ 26 ቀን 2014 ዓም በሰጠው ትዕዛዝ ይግባኙን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.337 መሰረት ሰርዞታል፡፡ተጠሪ በማስከትልም የሰበር ቅሬታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ.11306 አቅርበው ግራ ቀኙን አከራክሮ ህዳር 28 ቀን 2015 ዓም በሰጠው ውሳኔም በኪራይ ሰበብ ተከራዮችን በማስወጣት ወደ ቤቱ አመልካች በመግባት ግንባታ ስታከናውን ተጠሪ በቸልተኝነት መቆየቱ አግባብ ባለመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ.1180(2) መሰረት ዳኝነት የተጠየቀበትን ብር 600,000.00 1/4ኛ ግምት ሊከፍሉ ይገባል በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በዚህ ረገድ በማሻሻል ወስኗል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ አመልካችም በስር የቤንች ሸኮ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.11067 ቢያቀርቡም ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን አከራክሮ ሀምሌ 15 ቀን 2014 ዓም በሰጠው ውሳኔ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ያፀናው ሲሆን ይህ ውሳኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ.11792 ህዳር 28 ቀን 2015 ዓም በሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡

አመልካች በሰበር መዝገብ ቁጥር 239035 የሰበር ቅሬታቸውን ያቀረቡት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ.11306 አቅርበው ግራ ቀኙን አከራክሮ ህዳር 28 ቀን 2015 ዓም የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማሻሻል በሰጠው ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ሲሆን በሰ/መ/ቁ.239034 የሰበር ቅሬታቸውን ያቀረቡት ደግሞ የስር ፍርድ ቤት ከዋና ሁለት ደጃፍ ቤቶች አንፃር የሰጠው ውሳኔ በየደረጃው ባሉት ፍርድ ቤቶች በመፅናታቸው ቅር ተሰኝተው መሆኑን መዝገቡ ያሳያል፡፡

አመልካች የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ታህሳስ 18 ቀን 2015 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ በሰ/መ/ቁ.239034 ለዚህ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም፡ የስር ፍርድ ቤት የክልሉ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 75/96 ለተያዘው ጉዳይ ተፈፀሚነት የለውም፤ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የፍ/ብ/ህ/ቁ.712 ነው በማለት የደረሰበት ድምዳሜ ለህጉ አፈፃፀም መነሻ ሊሆን የሚገባው ግንኙነቱ የተቋረጠበት ጊዜ ሳይሆን የዳኝነት ጥያቄው የቀረበበት ጊዜ ከመሆኑ አንፃር ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የክልሉ ቤተሰብ ህግ መሆኑን የሚያሳይ ሆኖ እያለ በክልሉ የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 334 አዋጁን የሚቃረኑ ድንጋጌዎች ተፈፀማኒት የሌላቸው መሆኑ ተመልክቶ እያለ የፍ/ብ/ህ/ቁ.712 ለጉዳዩ ተፈፃሚነት አለው የሚል መደምደሚያ ላይ መድረሱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፤የፍ/ብ/ህ/ቁ.712 ከህገ መንግስቱ አንቀፅ 9 የሚቃረን፤በህገ መንግስቱ አንቀፅ 25፤34(1) እና 35 ሴቶች ከወንዶች ጋር በጋብቻ ጊዜና በፍቺ ጊዜ እንዲሁም በንብረት ማፍራትና በማግኘት ረገድ የጠበቀላቸውን የእኩልነት መብት የሚጥስ በሴቶች ላይ የሚደረግን ማንኛውንም አድሎአዊ ልዩነት ለማስወገድ የተደረገውን ስምምነት አንቀፅ 16(1)(ሐ)(ሸ) ከምክረ ሀሳቡ ቁጥር 21 አንቀፅ 32 እና 33 አንፃር ሲታይ ድንጋጌውን የሚቃረን በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት የፍ/ብ/ህ/ቁ.712 ን መሰረት በማድረግ የሰጠው ውሳኔ ተሽሮ በክልሉ የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 117 መሰረት ቤቱ የአመልካችና የተጠሪ የጋራ ሀብት ነው ተብሎ ሊወሰን ይገባል፤በቤቱ ላይ የተለያዩ ግንባታዎችን በማከናወን ግብር እየከፈልኩ፤በተጠሪ ስም የይዞታ ማረጋገጫ በማውጣት እንደ ባለመብት ተቀብዬ ሳስተዳድር እንደነበረ ተረጋግጦ እያለ ሁለት ደጃፍ ቤቱን የተጠሪ የግል ሀብት ነው ተብሎ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ውሳኔው ተሽሮ ሁለቱ ደጃፍ ቤት የጋራ ንብረታችሁ ነው ተብሎ ተወስኖ ክፍፍሉ በቤተሰብ ህጉ አንፃር እንዲፈፀም በቅድሚያ ግን በይዞታው ላይ ያከናወንኳቸውን ግንባታዎች የአመልካች የግል ሀብት ናቸው ተብሎ በቅድሚያ እንድወስድ ይወሰንልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ መቅረብ ያለበት መሆኑ ተገልፆ በሰበር አጣሪ ችሎቱ ወደ ሰበር ሰሚ ችሎቱ ከተመራ በኋላ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ንብረቱ በጋራ ያፈሩት ነው በማለት ካረጋገጠ በኋላ በወቅቱ እንደባልና ሚስት የመኖር ግንኙነት በንብረት ላይ ያለውን የህግ ውጤት በተመለከተ ህጉ ስላልወጣ ንብረቱ አይገባትም በማለት የወሰነበትን አግባብ ለማጣራት አቤቱታው ለሰበር ችሎት ይቅረብ፤ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ይቀባበሉ ሲል ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ለነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

አመልካች የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ታህሳስ 18 ቀን 2015 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ በሰ/መ/ቁ.239035 ለዚህ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከአንድ ውሳኔ ላይ የተነሱትን የሰበር ቅሬታዎች አጣምሮ አለመመልከቱ ሁለት የተለያዩ አይነት ውሳኔዎች እንዲሰጡ መነሻ የሆነ በመሆኑ ይኸው መሰረታዊ የክርክር አመራር ስህተት ሊታረም ይገባል፣አመልካች ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ በሰጠው ውሳኔ ቅር ተሰኝቼ በመ/ቁ.11067 ባቀረብኩት የይግባኝ ክርክር ላይ አቶ ምናሴ አሰፋ የተባሉ ዳኛ ተሰይመው የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ካፀኑ በኋላ ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ በሆነው የሰበር መዝገብ ላይ ተሰይመው የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ውሳኔ ማሻሻላቸው ፣በሰ/መ/ቁ.11792 ላይ የተሰየሙት አራት ዳኞች የከፍተኛ ፍርድ ቤቱን ውሳኔ ካፀኑ በኋላ በሰ/መ/ቁ.11306 ላይ ተሰይመው የከፍተኛ ፍርድ ቤቱን ውሳኔ ማፅናታቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው።

ለንብረቱ መፈራት መነሻ ከሆነው የግራ ቀኙችን ግንኙነት አንፃር የንብረት ባለቤትነቱ ጉዳይ መታየት ያለበት በቤተሰብ ህጉ መሰረት ሊሆን ሲገባ አመልካች ምንም መብት እንደሌለኝ ተቆጥሮ በሌላ ሰው መሬት ላይ ስለተሰራ ግንባታ ውጤት በሚደነግገው ለጉዳዩ አግባብነት በሌለው የፍ/ብ/ህ/ቁ.1179 እና 1180 አንፃር ታይቶ ውሳኔ መሰጠቱ አግባብነት የለውም፣የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት በማስረጃ አጣርተው ስለግንባታው ተጠሪ እውቅና እንዳለውና ምንም ተቃውሞ ሳያቀርብ አመልካች ግንባታ ማከናወኗንና ቤቱንም የሰራቸው በመካከላቸው በነበረው እንደባልና ሚስት የመኖር ግንኙነት መነሻ መሆኑን በማረጋገጥ የደረሱበትን መደምደሚያ ተጠሪ እውቅና እንዳለውና ግንባታውን እንድታካሂድ የሰጠው ፈቃድ ስለመኖሩ አመልካች ያረጋገጠችው ነገር የለም ማለቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው።

አመልካች በግሌ የሰራሁት ግምቱ ብር 600,000.00 የሆነ ሰርቪስ ቤትና የተለያየ ግንባታ የግል ንብረቴ እንዲባል ከመጠየቅ ውጪ ብር 600,000.00 እንዲከፈለኝ ያቀረብኩት የዳኝነት ጥያቄ በሌለበት የባለሙያው ግምት ከተጠየቀው ዳኝነት በላይ ነው በማለት ወደ ብር 600,000.00 ዝቅ አድርጎ ከዚህ ብር ላይ 1/4ኛውን ግምት ማስላቱ ስህተት ነው፣በማስረጃ ከተረጋገጠው አንፃር አመልካች ግንባታውን ያከናወነችው በጋራ ያፈራሁት ንብረቴ ነው መብት አለኝ በማለት ሆኖ እያለ ተጠሪም ማሻሻያ መደረጉንና አዲስ ግንባታ መገንባቱን እያወቀ ሳይቃወም መቅረቱ የፍ/ብ/ህ/ቁ.1180(2) ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት የሌለው መሆኑን እያሳየ ግምቱ ሊከፈላት ይገባል ከተባለ አግባብነት ያለው የፍ/ብ/ህ/ቁ.1179(2) ሆኖ እያለ በአንቀፅ 1180(2) መሰረት 1/4ኛ የዳኝነቱ ገንዘብ እንዲከፈለኝ መወሰኑ አግባብነት የሌለው በመሆኑ ሰበር ሰሚ ችሎቱ የሰጠው ውሳኔ ተሽሮ የስር ፍርድ ቤቶቹ ውሳኔ እንዲፀና ይወሰንልኝ በማለት አመልክተዋል።

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ለነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

አቤቱታው የቀረበለት የሰበር አጣሪ ችሎትም ከሰ/መ/ቁ.239034 ጋር ተያያዥነት ያለው ስለሆነ በጋራ እንዲጣሩ በማለት አቤቱታው ለሰበር ችሎት ይቅረብ፤ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ይቀጥበሉ ሲል ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ በሁለቱም መዝገቦች በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት መልሳቸውን በማጣመር መጋቢት 21 ቀን 2015 ዓም ያቀረቡ ሲሆን በዚህ መልሳቸውም፡-ቤቱ እንደ ባልና ሚስት የመኖር ግንኙነቱ በነበረው ወቅት መሰራቱ እንጂ በግንኙነቱ ወቅት በጋራ መስራታችን ሳይረጋገጥ ከዚህ ይልቅ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ቤቱ የግሌ መሆኑ ባረጋገጠበት፤አመልካች ከ1980 ዓም እስከ 1988 ዓም ድረስ አቶ አለሙ ከተማ ከተባሉ ግለሰብ ጋር ተጋብታ ስትኖር የነበረ መሆኑ መረጋገጡ በሰ/መ/ቁ.50580 በተሰጠው የህግ ትርጉም አንፃር ግንኙነቱ የህግ ጥበቃ የማይደረግለት ሆኖ እያለ አመልካች እንደ ባልና ሚስት የመኖር ግንኙነት አለን ብለው መጠየቃቸው አግባብነት የለውም፤በመሀከላችን እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት የሌለን መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ቤቱንም በጋራ መስራታችንን ያላስረዳች በመሆኑ ሁለቱ መኖሪያ ቤት የግል ሀብቱ ነው ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ ነው፡፡የአመልካችና ተጠሪ ግንኙነት ተቋርጧል በተባለበት ወቅት የክልሉ የቤተሰብ ህግ ወጥቶ በስራ ላይ ያልዋለ ሲሆን በአዋጁ አንቀፅ 335 በነባሩ ህጎች ተገኝተው የነበሩ ህጋዊ ሁኔታዎች ያስገኟቸው ውጤቶች ግንኙነቱ ከተቋረጠ በኋላ የወጣው አዋጅ ወደ ኋላ ተመልሶ የማይለውጣቸው መሆኑን የሚደነግግ በመሆኑ የፍትሐ ብሄር ህጉን ድንጋጌ መሰረት አድርጎ የስር ፍርድ ቤት መወሰኑ በአግባቡ መሆኑን ስለሚያሳይ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ተደርጎ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሊፀና ይገባል፡፡

ህጎች ተግባራዊነታቸው ወደፊት መሆኑን የህገመንግስቱ አንቀፅ 8 የሚደነግግ ሲሆን የቤተሰብ ህጉ ከጥቅምት 15 ቀን 1997 ዓም ጀምሮ ተፈፃሚነት ያለው መሆኑን አንቀፅ 138(2) የሚያሳይ በመሆኑ ፤ህገመንግስቱ ሴቶች ከወንዶች እኩል መሆናቸውን አስቀመጠ እንጂ ወንዶች በጎንዘባቸውና በልፋታቸው ያፈሩትን የሴቶች አስተዋፅኦ በሌለበት እኩል እንዲካፈሉና አላግባብ እንዲበለፅጉ የህግ ሽፋንን የሚሰጥ ባለመሆኑ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 34(1) የተመለከተው ሴቶች በጋብቻ ዘመን እና በፍቺ ጊዜ እኩል መብት እንዳለቸው የሚያረጋግጠው ጋብቻን አስመልክቶ እንጂ ከጋብቻ ውጪ በግብረስጋ ግንኙነት የሚኖሩትን የሚጨምር ባለመሆኑ፤ምክረ ሀሳቡም በተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባኤ ያልፀደቀ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 13(1) እና 9(1) መሰረት የህገ መንግስት ደረጃ ያልያዘ በመሆኑ አስገዳጅነት የሌለው በመሆኑ ተጠሪ ከከተማዬ ከወጣሁ 15 ዓመታትን ያስቆጠርኩኝ በመሆኑ ግንባታውን ልቃወም በማልችልበት ሁኔታ ውስጥ ስለነበርኩኝ ቤቱ በፍ/ብ/ህ/ቁ.708 እና 712 መሰረት ቤቱ የግል ሀብቴ ነው መባሉ በአግባቡ ነው፡፡በሰ/መ/ቁ.239035 ያለውን ክርክር አስመልክቶም ጉዳዮቹ ተጣምረው እንዲጣዩ ያልጠየቀች በመሆኑ፤አመልካች በይዞታዬ ላይ ስምምነት ሳኖር የገነባችውን በራሷ ወጪ አፍርሳ ልትለቅልኝ ሲገባ ብር 150,000.00 እንድከፍላት በመወሰኑ ተጠቃሚዋ አነልካች

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ለነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በመሆኗ፣ከዳኞች አሰያየም አንፃር ያቀረበችው ክርክርም አግባብነት የሌለው በመሆኑ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ተደርጎ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለመልኩ የተገለጸዉ የግራ ቀኙ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት የሚመለከት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት የያዘዉን ማስቀረቢያ ጭብጥ መሰረት በማድረግ በውሳኔው ላይ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡ከላይ እንደተመለከተው አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን በሰ/መ/ቁ.239034 ያቀረቡት አከራካሪዎቹ ሁለት ደጃፍ ቤቶች የተጠሪ የግል ሀብት ናቸው በማለት አመልካች ያቀረቡትን የተጋሪነት ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡በመሰረቱ አመልካችና ተጠሪ ከ1983 ዓም እስከ 1994 ዓም ከጋብቻ ውጪ እንደባልና ሚስት መኖራቸው፣አከራካሪዎቹ ሁለት ደጃፍ ቤቶች የተሰሩበትን ይዞታ ተጠሪ በ1982 ዓም በምሪት የወሰዱ ቢሆንም ቤቶቹ ከ1983 ዓም እስከ 1985 ዓም ባለው ጊዜ ውስጥ ተሰርተው ሲጠናቀቁ ግራ ቀኙ ከጋብቻ ውጪ እንደ ባልና ሚስት ሲኖሩ የነበረ መሆኑ ማስረጃን የመስማት፣የመመርመርና የመመዘን ስልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች ናቸው፡፡

ሴቶች ህገ መንግስቱ ባረጋገጣቸው መብቶችና ጥበቃዎች በመጠቀም ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት ያላቸው መሆኑን በማረጋገጥ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 35(1) መመልከቱ በጋብቻና መሰል የሕግ ውጤት ባላቸው ግንኙነት ውስጥ ያላቸውን የእኩልነት መብት እንዲሁም ንብረትን ከማፍራት፣ከማስተዳደር፣ከመቆጣጠርና ከማስተላለፍ ጋር በተያያዘ ያላቸውን የእኩልነት መብት የሚያሳይ በመሆኑ ይህ የእኩልነት መብት በራሱ ከንብረት ማፍራት ጋር በተያያዘ የተለየ አስተዋፅኦ በተለየ ሁኔታ ካልተረጋገጠ በስተቀር ያለምንም አድልዎ ተግባራዊ ሊደረግ የሚገባ መሆኑን ያሳያል፡፡

አከራካሪዎቹ ሁለት ደጃፍ ቤቶች ከላይ እንደተመለከተው ግራ ቀኙ ከጋብቻ ውጪ እንደ ባልና ሚስት ሲኖሩ የተገነቡ መሆናቸው መረጋገጡ አመልካችና ተጠሪ ሁለቱን ደጃፍ ቤቶች በተመለከተ በእኩልነት ሀሳባቸውን፣ጉልበታቸውን፣ጊዜያቸውንና ገንዘባቸውን በማውጣት ያፈሯቸው መሆናቸውን ያሳያል፡፡ከዚህ በተለየ ሁኔታ ተጠሪ የቤቶቹን ግንባታ በተመለከተ የተለየ አስተዋፅኦ ማድረጋቸውን ማስረዳታቸውን የስር ፍርድ ቤት መዝገብ አያሳይም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የስር ፍርድ ቤት ለጉዳዩ አግባብነት አለው በማለት የገለፀውን የፍ/ብ/ህ/ቁ.712 በተመለከተም ከህገ መንግስቱ በኋላ የወጣ ህግ ከህገ መንግስቱ ጋር የሚቃረን መሆን አለመሆኑ የሚመረመረው በፌዴሬሽን ምክር ቤት ቢሆንም ከህገ መንግስቱ በፊት የወጡ ህጎችን ከህገ መንግስቱ ጋር አጣጥሞ ስራ ላይ ማዋልም ሆነ መተርጎም መደበኛ ፍርድ ቤቶች ህገ መንግስቱን ከማክበርና ከማስከበር ሀላፊነታቸው ጋር የሚጠቃለል መሆኑ ከህገ መንግሰቱ አንቀፅ 13(1) ድንጋጌ የምንረዳው ነው፡፡በዚህም መሰረት የፍ/ብ/ህ/ቁ. 712 ከህገ

መንግስቱም ሆነ ከላይ ከተመለከቱት አግባብነት ካላቸው የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎች ጋር የማይስማማ ስለሆነ ይህን ድንጋጌ መሰረት በማድረግ አመልካች በአከራካሪው ቤት ላይ መብት የላቸውም የሚባልበት የህግ አግባብ አይኖርም፡፡ይህም ማስረጃን የመስማት፤የመመርመርና የመመዘን ስልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤቶች አከራካሪዎቹን ቤቶች በተመለከተ ለተጠሪ የተለየ የባለቤትነት መብት የሚያስገኝለት የሀሳብ፤የጉልበት፤የጊዜና/ወይም የገንዘብ አስተዋፅኦ መኖሩ ባልተረጋገጠበት የስር ፍርድ ቤቶች አከራካሪዎቹ ቤቶች የተጠሪ የግል ሀብት ናቸው ብለው መደምደማቸው ግንኙነቱ በተቋረጠበት ወቅት ተግባራዊ አፈፃፀም ያለውን የሕገ መንግስቱን አንቀፅ 35(1) እና በሴቶች ላይ የሚደረግን ማንኛውንም አድሎአዊ ልዩነት ለማስወገድ የተደረገውን ስምምነት 16(1)(ሸ) መሰረት ያላደረገ መደምደሚያ ላይ መድረሳቸውን ያሳያል፡፡

በአጠቃላይ አከራካሪዎቹ ሁለት ደጃፍ ቤቶች ሲሰሩ ግራ ቀኙ በህግ ጥበቃ በተሰጠው ከጋብቻ ውጪ እንደ ባልና ሚስት በመኖር ግንኙነት ውስጥ መኖራቸው በተረጋገጠበት፤ይህ ከሆነ ደግሞ ተቃራኒው በተጠሪ እስካልተረጋገጠ ድረስ ግንኙነቱን መሰረት አድርገው ግራ ቀኙ ቤቶቹን በጋራ እና በእኩልነት በተመሳሳይ ሀሳብና ፍላጎት ጉልበታቸውን፤ጊዜያቸውንና ገንዘባቸውን አውጥተው የሰሯቸው ናቸው ተብለው የሚታሰቡ ሆነው እያለ ተጠሪ ከዚህ በተቃራኒው አመልካች ቤቶቹ ሲገነቡ ምንም አይነት አስተዋፅኦ አለማድረጋቸውን ባላስረዱበት በቤቶቹ ላይ አመልካች ምንም አይነት ድርሻ የላቸውም፤ቤቶቹ የተጠሪ የግል ሀብት ናቸው በማለት የስር ፍርድ ቤቶች መደምደማቸው ለግራ ቀኙ ክርክር የህገ መንግስቱን አንቀፅ 35(1) ባገናዘበ መልኩ መፍትሄ አስቀምጠዋል የሚያስብል አይሆንም፡፡ይህም አከራካሪዎቹን ሁለት ደጃፍ ቤቶች የስር ፍርድ ቤቶች የደረሱበት መደምደሚያ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት መሆኑን ያሳያል፡፡

በሰ/መ/ቁ.239035 የቀረበውን የሰበር ክርክር አስመልክቶም በመሰረቱ አንድ ዳኛ ቀድሞ ውሳኔ የሰጠበት ጉዳይ በሌላ ፍ/ቤት/ችሎት በተለይም በይግባኝ ችሎት በሚቀርብበት ጊዜ በድጋሚ ተሰይሞ ማየት የለበትም ተብሎ በዳኞች የስነምግባር ህጎች ተደንግጎ የሚገኝበት ዋነኛው ምክንያት በፍ/ቤቶች የሚሠጡ ውሳኔዎችን በየደረጃው በሚገኙ የይግባኝ/ ሰበር ሰሚ ፍ/ቤቶች በማቅረብ የማሳረምና ፍትህ የማግኘት መሰረታዊ የሰው ልጆች መብት ከመሆኑ አንፃር ይህን መተግበርም የተሻለ/ የተለየ የህግ አተረጓጎም አረዳድ/ ችሎታን በእጅጉ የሚጠይቅ መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ የይግባኝ መሰረታዊ አላማም ይኸው ነው፡፡ በመሆኑም አንድ ዳኛ ቀድሞ ውሳኔ የሰጠበትን ጉዳይ ደግሞ በይግባኝ በሚያይበት ጊዜ ጉዳዩን ቀድሞ ካየበት አረዳድ በተለየ ሁኔታም ሆነ ከቀድሞ ውሳኔው ገለልተኛ በሆነ ሁኔታ ለማየት ይችላል ተብሎ የማይገመት በመሆኑና ለይግባኝ የሚቀርቡ ጉዳዩችም ቀድሞ ጉዳዩን ካየው ዳኛ የተለየ/ የተሻለ የህግ አተረጓጎም ችሎታና ልምድ ያላቸው ዳኞችን የሚጠይቅ እንደመሆኑ መጠን አንድ ዳኛ ቀድሞ አይቶ ውሳኔ የሰጠበት ጉዳይ በይግባኝ ሲቀርብ

ደግሞ አይቶ የሚወስን ከሆነ መሰረታዊ የሆነውን በይግባኝ ፍትህ የማግኘት መብትንም ሆነ ዋነኛውን የይግባኝ አላማ የሚቃረን (self-defeating) ነው፡፡

አሁን በያዝነው ጉዳይ አመልካች በሰ/መ/ቁ.239035 የሰበር ቅሬታቸውን ያቀረቡት አመልካች ያቀረቡትን የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አስመልክቶ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ.11306 በ28/03/2015 ዓም በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ነው፡፡በሰ/መ/ቁ.11306 ለተሰጠው ውሳኔ መነሻ በሆነው በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.10947 በ26/08/2014 ዓም በተሰጠው ውሳኔ ላይ ዳኛ ምናሴ አሰፋ ተሰይመው ፍርድ ያልሰጡ ቢሆንም ተጠሪ ያቀረቡትን ክስ መነሻ ባደረገው በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.11067 በ15/11/2014 ዓም በተሰጠው ውሳኔ በዳኝነት ተሰይመው ስለ ክርክሩ የቀደመ እውቀት ይዘው ተገቢ ነው የሚሉትን ውሳኔ ከሰጡ በኋላ ከተመሳሳይ የስር የቤንች ሸኮ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ በመነጨው በሰ/መ/ቁ.11306 በተሰጠው ውሳኔ ላይ በዳኝነት ተሰይመው ፍርድ መስጠታቸው በሰ/መ/ቁ.11306 ስለተደረገው ክርክር ተገቢውን የቀደመ እውቀት ይዘው በተመሳሳይ ጉዳይ ውሳኔ ሰጥተው በሰ/መ/ቁ.11306 የምርመራ እና ውሳኔ አሰጣጥ ላይ በዳኝነት መሳተፋቸውን ያሳያል፡፡የሰበር ክርክሩ ስለጉዳዩ የቀደመ እውቀት በሌላቸውና ለጉዳዩ ገለልተኛ በሆኑ ዳኞች ጉዳዩን በገለልተኝነት ታይቶ ተገቢው እልባት ሊሰጠው ሲገባ ከህጉ አግባብ ውጪ ስለጉዳዩ የቀደመ እውቀትና ግንዛቤ በአንዳንድ ሁኔታዎችም መደምደሚያን የያዘ ዳኛን በማካተት በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ለግራ ቀኙ ክርክር ፍርድ መሰጠቱ ከክርክር አመራር ስነስርዓት አንፃር ጉልህ ግድፈት መፈፀሙን ስለሚያሳይ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ውሳኔ

1. የቤንች ሸኮ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.20911 በ09/06/2014 ዓም ክርክር ያስነሳው ሁለት ደጃፍ ቤት የተጠሪ የግል ሀብት ነው በማለት የሰጠው የውሳኔ ክፍልና ይህንን የውሳኔ ክፍል በማፅናት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/መ/ቁ.11067 ሀምሌ 15 ቀን 2014 ዓም እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ.11792 በ28/03/2015 ዓም የሰጡት ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በሰሜን መንገድ፤በደቡብ አቶ ኢብራሂም፤በምዕራብ ካሳዬ እና በምስራቅ መንገድ የሚያዋስነው ሁለት ደጃፍ ቤት የግራ ቀኙ የጋራ ሀብት ነው ብለናል፡፡ቤቱ በአይነት ሊካፈል የሚችል ከሆነ ግራ ቀኙ በአይነት እንዲካፈሉ፤በአይነት መካፈል ካልቻለ በስምምነት አንደኛው ወገን የአንደኛውን ወገን ድርሻ ከፍሎ እንዲያስቀረው፤በዚህ ካልተስማሙ በስምምነት ሸጠው እንዲካፈሉ፤በዚህም ካልተስማሙ ቤቱ በሀራጅ ተሸጦ የሽያጩን ገንዘብ ግራ ቀኙ እኩል እንዲካፈሉ ተወስኗል፡፡
3. የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጲያ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 11306 በ28/03/2015 ዓም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
4. የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጲያ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በፍርድ የዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ በዳኛ ምናሴ አሰፋ ምትክ ጉዳዩን አስቀድመው

ያላዩና ስለጉዳዩ የቀለመ እውቀት የሌላቸውን ገለልተኛ የሆኑ ዳኛ እንዲሰየሙ በማድረግ ጉዳዩን እንደገና አይቶ የመሰለውን ውሳኔ እንዲሰጥ መልሰንለታል፡፡

5. በቤንች ሸኮ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.20911 በተጀመረው አፈፃፀም ላይ በ20/06/2015 ዓም ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
6. ግራ ቀኙ በሰበር ክርክሩ ምክንያት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
7. በዚህ መዝገብ የተሰጠው ውሳኔ ከሰ/መ/ቁ.239035 ጋር እንዲያያዝ ታዟል፡፡

<u>ጉዳዩ ውሳኔ ስላገኘ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡</u>

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/ት